ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 138 እንደተመለከተው የደረጃ እድገት ይሰጠኝ ጥያቄ ወይም ክስ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚካተት አይደለም፡፡ ይህም ማለት ተጠሪ ለወረዳ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ያቀረበው ክስ ከመሰረቱ መቅረብ የሚችል አልነበረም ማለት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ባለማየት የተጠሪን የእድገት ጥያቄ በመቀበል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአርሲ ዞን ጢዮ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 07193 ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13157 ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም በተሰጠው ብይን የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በቋሚነት እንዲሰጠው የጠየቀውን የደረጃ እድገት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሻሩ ይታወቅ ዘንድ ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰበር መ.ቁ. 34585

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሠ
መድህን ኪሮስ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ተስፋዬ ኬርጋ

ተጠሪ፡- ደረጀ ወልደኪዳን ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ በሆነ ሁኔታ ተቋረጠብኝ በማለት ሲሆን፣ ወደስራው እንዲመለስ፤ ይህ ካልተቻለም ተገቢ የሆኑት ክፍያዎች ተከፍለውት ይሰናበት ዘንድ እንዲወሰንለት ጠይቆአል፡፡ አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተው በተቀጠረበት የጥበቃ ስራ ላይ ተመድቦ በመስራት ላይ እንዳለ የሥርቆት ተግባር ሲፈጽም በመገኘቱ እንደሆነ በመግለጽ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን መርምሮ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ የሁለት ወር ደመወዙ ተከፍሎት ወደስራው ይመለስ ዘንድ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የስርቆት የሙከራ ወንጀል ፈጽሞአል ቢባልም፤ ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነፃ ተለቆአል በሚል የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ይዘት እና ከግራ ቀኝ ወገኖቹ ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ በጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርቶ በነበረበት ዕለት ስምንት ጀሪካን የትራንስፎርመር ዘይት ሞልቶ ሊያወጣ /ሊወስድ/ ሲል በድርጅቱ ስራ አስኪያጅ እና ሠራተኞች ስለመያዙ በማስረጃ ተረጋግጦአል፡፡ ፍ/ቤቱ በተጠሪ ላይ የተወሰደው የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ ከሕግ ውጪ ነው ለማለት የበቃው ተጠሪ የመስረቅ ሙከራ ተግባር ለመፈፀሙ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ሣይሆን፣ የወንጀል ክስ ቀርቦበት በነፃ ተሰናብቶአል፣ ድርጊቱ ከሙከራ ያላለፈ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ የራሱ ያልሆነውን ንብረት ሠርቆ ለመውሰድ ሲል እጅ ከፍንጅ ስለመያዙ በማስረጃ ተረገግጦአል፡፡ ይህን መሰሉ የስርቆት ተግባር ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ከሚያሰናብቱ ምክንያቶች አንደኛው እንደሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27 ተመልክቶአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሕጉ እንዲህ የሚል ስለመሆኑ ግንዛቤ መውሰዱን በውሣኔው ላይ ገልጾአል፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ ሌላው በወንጀል ክሱ ተጠሪ ጥፋተኛ አልተባለም የሚለው ሲሆን፣ ይህም በፍትሐብሔር ረገድ ለቀረበው ክርክር ያለውን አግባብነት በሚገባ ማየት ያስፈልጋል፡፡ እንደሚታወቀው



የወንጀል እና የፍትሐብሔር ክርክሮች ራሣቸውን ችለው የሚታዩ ናቸው፡፡ በማስረጃ ምዝና ረገድም የየራሣቸው አካሄድ አላቸው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው በወንጀል ጥፋተኛ ያልተባለ ሰው በፍ/ብሄር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ለማለት የማይቻል እንደሆነ ነው፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ፈጽሞታል የተባለውን የስርቆት ወንጀል በእርግጥም ስለመፈፀሙ ክሱን በሰማው የስራ ክርክር ችሎት ተረጋግጦአል፡፡ ችሎቱ በራሱ ይህን ካረጋገጠ ደግሞ በወንጀል ክሱ ወደተሰጠው ውሣኔ የሚሄድበት ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ የፈፀመው ድርጊት በሕጉ ብቻ ሣይሆን፣ በህበረት ስምምነቱም ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብት እንደሆነ ነው ለመገንዘብ የቻልነው፡፡ ስናጠቃልለው አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርጎት የነበረውን የስራ ውል ያቋረጠው በሕጉ መሠረት በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.18281 ሚያዝያ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 55472 ታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ